# አንድነት ሰሜን አሜሪካ የድጋፍ ድርጅቶች ማሕበር

**ANDINET NORTH AMERICA ASSOCIATION OF SUPPORT ORGANIZATIONS (ANAASO)**

1334 9th Street, NW. Suite # 1 Washington DC. 20001.
Tel: (202) 462 0556 Fax: (202) 462 0557 Email: info@andinetusa.org


## *ትግሉ ሲገፋ ፤ ወያኔ ፈራ!!!*

እነደ ወያኔ ፍላጎት ቢሆን ኖሮ፤ እንደነሱማ ምኞት፤ የኢትዮጵያን ትግል፤ የህዝቡን የነፃነት ተጋድሎ፤ ለፍትህና ዲሞክራሲ የሚደረገውን ትንቅንቅ ቀጭተውት ነበር። ከ97ቱ ምርጫ በህዋላ፤ መሰለፍ ክልክል ነው፤ መቃወም አይቻልም፤ መሰብሰብ አይሞከርም፤ ዋ ትቃወሙና፤ ጣት ብትቀስሩ ውርድ ከራስ በማለት፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ የሰው አይሉት የአራዊት፤ ጫካ የለመዱትን አዋጅ ደረደሩ። እንደሳቸውና እንደጀሌዎቻቸው፤ ህዝብ ይፈራል፤ ነፍጥ ያይላል፤ ወያኔም ለመቶ አመት ይነግሳል።

በ97ቱ ምርጫ፤ እነደ ሩቅ ኮከብ፤ በተስፋ ሰጭነት ብልጭ ብልጭ፤ ብሎ የነበረው፤ የዲሞክራሲ ጅማሮ፤ ነፃ ፕሬስን በማፈን፤ ማንበብና መጻፍን በመከልከል፤ ፍትህን የፖለቲካ መሳርያ በማድረግ፤ ምርጫ ቦርድን የኢህአዴግ ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ድረጅት በማድረግ፤ አጋዚ ጦርን በብርጌድ በብርጌድ ከፋፍሎ፤ ህዝብ ላይ በማዝመት፤ አስሮ አሳዶ ገድሎ፤ የተስፋዋን ብርሃን ድብዝዝ አደረጉት።

ይህም አልበቃ ብሎ፤ ኢትዮጵያን ሀገራችንን፤ እምዬን፤ ከአንድ ድንበር ወደ ሌላ፤ ከሰሜን ወደ ምስራቅ፤ ከዚያም ወደ ምዕራብ፤ በሚያገባን በማያገባን ሁሉ ከዚህም ከዚያም ጎረቤት ሀገር አጋጩን። ጦር ሰብቀው በሶማሊያ የውክልና ጦርነት ያዙ፤ ባድመን ስጥ ሰልሰጥም፤ ከኤርትራ ጋር ጦርነት አይሉት ሰላም አይሉት ተፋጠጡ።

በሀገር ውስጥ፤ በተሳሳተና ህዋላ ቀር የኢኮኖሚ ፖሊሲ፤ የህዝቡን ንብረት ማፍራትና ሰርቶ የማደር መብት ነፈጉ። ዕውቀትና ሙያ የጎደላቸው፤ የገዥው ፓርቲ አጎብዳጆች እንደ አዲስ መደብ ተፈለፈሉ። ኢኮኖሚው ቁልቁል ተወረወረ፤ ዋጋ ሽቅብ ተወነጨፈ። የሥራ አጥ ቁጥር ተሰምቶ የማያውቅ ሆነ። ለነገ ማለት ቀርቶ፤ በልቶ ማደር፤ መታደል ሆነ።

ሃፍረት የሚባል እልፍም ያላለባቸው ወያኔያውያን፤ ሁሉ ሞልቶ ሁሉ ተርፎ፤ ኢኮኖሚያችን እያደገ ነው አሉ። ስለዚህም የኢትዮጵያን ህዝብ በምርጫ ምረጠን አሉት። ሥራ ለማግኘት፤ ለመነገድ፤ ለማረስ፤ በልቶ ለማደር፤ እነሱን መምረጥ፤ እልፍ ሲልም 'አባላቸው' መሆን ግዴታ ሆነ። አራት ሚሊዮን አባላት አሉኝ አሉ፤ በየቀበሌውም ተመረጡ ተባለ።

በአንፃሩ፤ የህዝብ ጥሪ ትግል የሚል ነው። ተደራጁ፤ ታገሉ አታግሉን። ድርጅት፤ ህዝባዊ ድርጅት። አንድነት ለፍትህና ለዲሞክራሲ / አንድነት/ ፓርቲ፤ በ97 ህዝባዊ እንቅስቃሴ፤ ፋና ወጊ የነበረው የቅንጅት፤ የህግና የሞራል ወራሽ ሆኖ ብቅ አለ። መርሃችን በኢትዮጵያ ውስጥ ሰላም፤ ዲሞክራሲ፤ ፍትህ፤ የህግ የበላይነትን ማስፈን ነው አሉ። አላማችን የበለፀገችና በዓለም ህዝብ የተከበረች ኢትዮጵያን መገንባት ነው አሉ። ለዚህም ሰላማዊና ህጋዊ በሆነ ትግል፤ ህዝብን እነመራለን አሉ።

ገዥው ፓርቲ፤ ህዝቡን አፍኛለሁኝ፤ ህዝብ ፈርቷል፤ የህዝብ ትግል፤ የህዝብ ድርጅት ብዙም አይራመድም ሲል አሰበ። በየመንገዱም፤ በሂደቱም፤ ተልካሻ፤ አንዳንዴም አስቂኝ ሰበቦችን በመደርደር፤ ለማደናቀፍ ሞከረ። በጎጃም

ህዝብ ለማደራጀት፤ በህዝብ ጥሪ የተንቀሳቀሱትን ኢንጅነር ግዛቸው ሽፈራውንና አብረዋቸው የተጓዙትን ሁለት የፓርላማ አባላት ለሰዓታት አሰረ። የፓርላማ አባላት ያለመከሰስ መብት ለወያኔ ምኑም አይደለም። በመቱ የአከባቢውን የአንድነት ፓርቲ ተመራጮችን አሰረ፤ ለምን ብለው ለመጠየቅ የሄዱትን ዶ/ር ሀይሉ አርአያን መኪና መስተዋት አሰበረ። ለአንድነት ፓርቲ ፅ/ቤት ለማከራየት የደፈሩትን አዋከበ፤ አስጠነቀቀ። የፈሪ ዱላው፤ ከህግ በላይ የሆነበት ዱላው በየአቅጣጫው ተወናጨፈ።

ይሁንና፤ የትግሉ አቅም የሚለካው፤ ውጤትም የሚያመጣው፤ በኢህአዴግ ጉልበት ሳይሆን በህዝብ ጥንካሬ ላይ ነው ያለው አንድነት፤ በህዝቡም እምነት ያሳደረው አንድነት፤ በተራው የህዝብን ዕምነት እሱም አገኘና፤ ወፌ ቆመች እየተባለለት፤ አንድ ሁለት በማለት፤ ለወያኔ አስጊ እየሆነ መጣ። ትግሉ ሲገፋ፤ ወያኔ ፈራ!!!

ለዚህም ነው ከሰሞኑ ደግሞ፤ ዲሞክራሲያው በሆነ የውስጥ አሰራር፤ ፍፁም ግልፅ በሆነ ምርጫ፤ ሊቀመንበር በመሆን የተመረጡትን፤ ወ/ት ብርቱካን ሚዴቅሳን፤ ማዋከብን የመረጡት። ባለፈው ሰሞን፤ ትንሹ ሚያዝያ 30፤ የተባለለትን የመጀመርያ ህዝባዊ ስብሰባ አንድነት ፓርቲ በተሳካ ሁኔታ ካካሄደ ወዲህ፤ ሌሎችንም ህዝባዊ ስብሰባዎች በተመሳሳይ በተለያዩ ከተሞች ለማድረግ ማቀዱን ግልፅ ካደረገ ወዲህ፤ አዲስ የማዋከብ ዘመቻ ወያኔ የከፈተው።

ወ/ት ብርቱካን የፖሊስ መጥሪያ አልደረሳቸውም፤ ይህ ህጋዊ አይደለም። የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽነር እንደሚፈልጓቸው ይገለፅላቸዋል። በኮሚሽነሩ ፅ/ቤትም አንድ ሌላ ማንነታቸው ያልተገለፀላቸው ግለሰብም ነበሩ። ይህም ህጋዊ አይደለም። ኮሚሽነሩ የወ/ት ብርቱካንን ቃል ተቀብለው፤ ለበላይ አካል አስተላልፈን ውጤቱን እናሳውቃለን አሉ፤ ይህ ደግሞ አጠራጣሪ ነው።

ዞሮ ዞሮ ግን፤ የዚህኛው የማዋከብ ዓላማ ምንድነው የሚል ጥያቄ ያስነሳል። ወ/ት ብርቱካን ከአውሮፓው ጉብኝታቸው በህዋላ ወደ ሀገር ቤት አይመለሱም የሚል መሰረተ-ቢስ ወሬ ሲናፈስ ከርሟል። ምናልባት፤ የወያኔ ምኞት ሆኖ ሊሆን ይችላል። ወ/ት ብርቱካን የፓርቲው ቁርጠኛ ታጋይ፤ ፅኑ ዓላማ ያላቸው፤ የህዝብ አይን መሆናቸውን ያለጥርጥር አውቆታል። ስለዚህም፤ ማስፈራራትና ማስጠንቀቅን እንደ ዘዴ የያዘው ይመስላል። ወያኔ ያላወቀው ግን፤ ወ/ት ብርቱካንና የአንድነት ጓዶቻቸው፤ ትግሉ የሚጠይቀውን መስዋእትነት ጥልቀትና ውርደቱን ጠንቅቀው የሚያውቁ፤ እጅ ለእጅ ተያይዘው፤ አንዱ ለሁሉም፤ ሁሉም ለአንዱ የቆሙ፤ ከሁሉም በላይ ደግሞ ህዝብን አቅፈው በህዝብ ታቅፈው የሚጓዙ፤ የህዝብ ልጆች መሆናቸውን ነው። እዚህ ላይ በ97ቱ ምርጫ ወቅት አንድ የኬንያ ጋዜጠኛ የፃፈውን እንድገመው፤ "... ህዝቡን ሁሉ ለማሰር በቂ እስር ቤት፤ ህዝቡን ሁሉ ለመግደል በቂ ጥይት የለም... "። የህዝብ የነፃነት ትግል፤ የተፈጥሮ ትግል ነው። የትግሉ ጥንካሬ የሚለካውም በወያኔ ጉልበት ሳይሆን በህዝብ ጥንካሬ ነው። ትግሉ የሚደመደመው፤ ወያኒ ፈርቶ ሲያስፈራራ፤ ሲያስርና ሲገድል ሳይሆን፤ ህዝቡ በትግሉ ነፃነቱን ሲጎናጸፍ ብቻ ነው።

እኛም በሰሜን አሜሪካ የምንገኝ የአንድነት ፓርቲ ድጋፍ ሰጭ ማህበር አባላት፤ በዚህ አጋጣሚ፤ ሀገር ቤት ለሚገኘው አንድነት ፓርቲ የትግል አንድነታችንና ቁርጠኝነታችንን ያለማወላወል ለመግለፅ እንወዳለን።

***በሰሜን አሜሪካ የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ድጋፍ ሰጭ ማህበር***